ማኅበራዊ ጥናት መድረክ
Forum for Social Studies

ነሐሴ 2000 ዓ.ም. — የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች — ቁጥር 17

# የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብትና የአካባቢ እንክብካቤ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና መርሐግብሮች

- የማኅበራዊ ጥናት መድረክ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ-ነክ ምርምሮችን የሚያደርግ ለትርፍ ያልተቋቋመና መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ነው።

❈❈❈

- የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል።

❈❈❈

- በአዲስ አበባ (በ97.1 ሞገድ) እና በአዋሳ (በ100.9 ሞገድ) ከተሞች ኤፍ.ኤም. ራዲዮ ጣቢያዎች ልማት ነክ ጉዳዮችን እያዘጋጀ ያሰራጫል።

❈❈❈

- በድረ-ገጹ በልማት ዙሪያ ውይይቶችን ያካሂዳል።

❈❈❈

- በርዕሱ ዙሪያ ሐሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜይል አድራሻችን ላኩልን።

## 1. ዓላማ

ይህ ጽሑፍ በኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብትና የአካባቢ እንክብካቤ (በደን፣ በዱር እንስሳት በውሃ፣ በአካባቢ ጥበቃና በመሬት አስተዳደር) ፖሊሲዎችን፣ ሕጎችንና መርሐግብሮችን ከሚፈትሽውና ዓላማዎቻቸውንና ዋና ዋና ይዘታቸውን፣ እንዲሁም በይዘታቸውና በአፈፃፀማቸው የታዩ ጠንካራና ደካማ ጐኖችን በመለየት መፍትሔ ለመጠቆም ከተሞከረበት ሰፋ ያለ የዳሰሳ ጥናት የተወሰደ ፍሬ ሀሳብ ነው። ጽሑፉ የፊውዳሉንና የደርግን ሥርዓት ዘመን እንደመንደርደሪያ ብቻ በመውሰድ እ.ኤ.አ. ከ1991 የመንግሥት ለውጥ በኋላ ባሉት ፖሊሲዎች ላይ ያተኩራል።

## 2. ከፊውዳሉ ዘመን እስከ ደርግ መውደቅ

ከተፈጥሮ ሀብቶች መካከል የደን ሀብትን የተመለከተ ለመጀመያ ጊዜ ዘመናዊ ሊባል የሚችል የፖሊሲ፣ የህግና መርሐግብር የወጣው ጣልያን ኢትዮጵያን በወራሪነት በያዘችበት ጊዜ በ1937/38 እ.ኤ.አ. ነበር። ጣልያኖች ሰፊ የደን አስተዳደር መዋቅር በመዘርጋት ከ20 በላይ የፖሊሲ መመሪያዎችንና ደንቦችን ያወጡ ቢሆንም በጊዜው ትኩረታቸው የነበረው በመጠቀም ላይ ብቻ ነበር። እ.ኤ.አ. የ1931 ሕገ መንግሥት ስለተፈጥሮ ሀብት ይዞታና አጠቃቀም የጠቀሰው አንዳች አንቀጽ ባይኖርም እ.ኤ.አ. የ1995 ህገ መንግሥት ግን አጠቃቀማቸው ሁሉንም ዜጋና መጪውንም ትውልድ እንዲያገለግሉ ተገቢውን እንክብካቤ በማድረግ ላይ እንደሚመሠረት ይደነግጋል። እ.ኤ.አ. እ.ኤ.አ. በ1940ዎቹ የዱር እንስሳትን አደን በተመለከተ ሕግ ያወጣ ሲሆን ከ3.4 ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት ጥብቅ የዱር አራዊት ክልል እንዲሆን ተደንግጓል። እ.ኤ.አ. በ1952/53 በግብርና ሚኒስቴር ተረቀው የቀረቡት የመንግሥት፣ የግል እና ጥብቅ ደንን የተመለከቱ ሦስት ረቂቅ ህጐችን ፓርላማው «በግል ንብረት ላይ ጣልቃ መግባት ነው» በሚል ውድቅ ቢያደረጋቸውም ከ12 ዓመታት ያህል በኋላ ተሻሽለው ፀድቀዋል። እ.ኤ.አ. በ1965 የፀደቁት ህጐች እ.ኤ.አ. በ1968 ደንብ ወጥቶላቸው እ.ኤ.አ. በ1972 አስፈፀሚ አካል እስኪመሠረት የፊውዳሉ ሥርዓት ለውድቀት የቀረው ጊዜ ሁለት ዓመት ያህል ብቻ ነበር። ይህ ወቅት በጣልያኖች 6 ሚሊዮን ሄክታር ተገምቶ የነበረው የደጋ ደን ወደ 3 ሚሊዮን ያሽቆለቆለበት፣ የደን መሥሪያ ቤት ባለሙያዎች የተበተኑበት እና የደን የዲፕሎማ ስልጠና የተቋረጠበት ነበር።

እ.ኤ.አ. በ1975 የገጠርና የከተማ መሬትና ትርፍ ቤቶች በአዋጅ የመንግሥት ይዞታ ሥር መግባት በተፈጥሮ ሀብት ባለቤትና አጠቃቀም ላይ ከፍተኛ ለውጥ አስከትሏል። በፊውዳሉ ዘመን በጥቂት ግለሰቦች በከፈተኛ ደረጃ ይመዘበር የነበረው የተፈጥሮ ደን ፋታ የሚያገኝ ቢመስልም በግል የለሙ ደኖች መወረስና የመሬት ይዞታ ዋስትና ማጣት፣ እንዲሁም ተከታትለው የመጡት የመንደር ምስረታ፣ የህብረት እርሻና የሰፈራ የገጠር ልማት ፕሮግራሞች ወዘተ. በተፈጥሮ ሀብት ልማትና የአካባቢ እንክብካቤ የግለሰቡን ሚና በእጅጉ አሳስተውት ቆይተዋል። እ.ኤ.አ. በ1980 ዓ.ም. የወጣው የደን አዋጅ “Forest Priority Areas” ተብለው ለተሰየሙት ደኖች ወሰን ለመከለልና የተከላ ሥራዎችንም ለማካሄድ መነሻ ሆኖ አገልግሏል። በገጠር ቀበሌዎች ሥር የነበሩትን የደን ሥራዎች ወደ መንግሥት ይዞታ በማዛወር የተወሰደው እርምጃ በመንግሥትና በደን ዙሪያ በሚኖረው ህብረተሰብ መካከል አሁንም የሚታይ የጥቅም አለመግባባት እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል።

## 3. የተፈጥሮ ሀብትና የአካባቢ እንክብካቤ እ.ኤ.አ. ከ1991 ወዲህ

እ.ኤ.አ. በ1991 የተደረገው የመንግሥት ለውጥ ምንም እንኳ በመሬትና በተፈጥሮ ሀብቶች የንብረት ግንኙነት ላይ መሠረታዊ ለውጥ ባያመጣም የኢኮኖሚውና የአስተዳደር ፖሊሲዎቹ ከነበረው የተማከለ የአስተዳደርና የኢኮኖሚ ሥርዓት የተለዩ በመሆናቸው በተፈጥሮ ሀብቱ አያያዝ ለውጥ ማስከተላቸው አልቀረም። በደርግ ዘመን

ተዘርግቶ የነበረው የተማከለ የተፈጥሮ ሀብት አስተዳደር ጥበቃ በድንገት በመፍረሱ በተፈጠረው ክፍተት በተፈጥሮ ሀብት ላይ ጉዳት ደርሷል፡፡ ይህን ለመቋቋም በማሰብ እ.ኤ.አ. እስከ 2007 ድረስ የወጡት የአካባቢ እንክብካቤ ፖሊሲዎች፣ ሕጐችና መርሐግብሮች ከዚህ በታች በአጭሩ ቀርበዋል፡፡

## 3.1 የኢትዮጵያ ደን መርሀ ግብር (EFAP፣ 1994)

መነሻው የደርግ (1984-94 እ.ኤ.አ.) የደን ልማት ዕቅድ የሚመስለው ይህ ሠነድ በ12 ግብረ ኃይሎች በ3 የሥራ ቡድኖችና በዓለም አቀፍ አማካሪዎች ትብብር የተዘጋጀ ሠነድ ነው፡፡ ከአላማዎቹ መካከል የደን ልማትን በዘላቂነት ማከናወን፣ የአፈር መከላትን መከላከልና ምርታማነቱን መጨመር፣ ብዝሃ ሕይወትን መጠበቅ የሚሉ ሲሆን መርሐ ግብሮቹም የዛፎችና የደን ምርት ዕድገት፣ የደን ሀብትና ኢኮሲስቴም እንክብካቤ፣ የደን ኢንዱስትሪዎች ልማትና ከእንጨት የሚገኝ ኃይል ልማትን ያጠቃልላል፡፡ ሠነዱ የሀገሪቱ ደንና ተዛማጅ ዘርፎችን ትስስር ያገናዘበ የደን ልማት አሳታፊ የመሆኑን አስፈላጊነት የመረመረ የተሟላ ሠነድ ነበር፡፡ ይሁንና ሠነዱ እንደሚጠቁመው የፕሮግራሞቹ ተግባራዊነት የሚወሰነው የኢኮኖሚ፣ የመሬት ይዞታና የሥነ ሕዝብ ፖሊሲዎች አስፈላጊ ክለሳ ሲደረግላቸው እንደሆነ ያብራራል፡፡ ሠነዱ የተጠቀመባቸው መረጃዎች የቆዩ መሆናቸው እንደ አንድ ድክመቱ ሊቆጠር ይገባል፡፡

## 3.2 የኢትዮጵያ ሀብት ጥበቃ ስትራቴጂ (እ.ኤ.አ.1997)

ይህ ባለአምስት ቅፅ ሰነድ በ11 ዘርፎችና ተመሳሳይ ቁጥር ባላቸው ዘርፍ-ዘለል ክፍሎች የተሰናዳና የመንግሥት የተፈጥሮ ሀብትና የአካባቢ እንክብካቤ ፖሊሲ መሠረት ያላቸውን 19 ዋና ዋና መርሆዎች የያዘ ነው፡፡ ከመርሆዎቹም መካከል የሰዎች በጤናማ አካባቢ የመኖር መብት፣ የአካባቢ ብክለት ቅነሳ፣ የህብረተሰቡን ተሳትፎ፣ የባለቤትነት ይዞታን ማረጋገጥ፣ የብዝሃ-ሕይወት እንክብካቤ ወዘተ ይገኙበታል፡፡

### 3.3 የኢትዮጵያ አካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ (እ.ኤ.አ. 1997)

ከዓላማዎቹ መካከል የተፈጥሮ ሀብትን ዘላቂ ጥቅም ሰጪነት ማረጋገጥ፣ በጥቅም ላይ ያልዋለ ሀብትን መጠቀም፣ ለሰዎች መኖሪያ እንክብካቤ ማድረግ፣ የውሃ፣የመሬት፣አፈርና የአየር ብክለትን መከላከል፣ ባሕላዊ ቅርሶችን መጠበቅ፣ በአካባቢ ጉዳዮች የህዝቡን ተሳትፎና ግንዛቤ ማሳደግ የሚሉ ይገኙበታል፡፡ ሰነዱ ለፖሊሲው ተግባራዊነት መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የማህበረሰቡ ተወካዮችና የሙያ ማህበራት ተሳትፎ አስፈላጊነትን በመቀበል ያልተማከለ አስተዳደር መፍጠር ዘርፋዊ ፍላቶችን በማጣጣም የኢኮኖሚ ልማት ዕቅዶችን ከአካባቢ እንክብካቤ ጋር ማዋሀድ እንደሚገባ ይቀበላል፡፡

## 3.4 የኢትዮጵያ የውሃ ፖሊሲና ስትራቴጂ (1994 እ.ኤ.አ.)

ይህ ፖሊሲ የውሃ ሀብት የህዝብ መሆኑን መነሻ በማድረግ ሀገሪቱ ያላትን የውሃ ሀብት አጠቃቀም ምርታማ፣ ፍትሐዊና ሚዛናዊ ማድረግ ዓላማው መሆኑን ያወሳል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሠነዱ ከውሃዎች አስተዳደር፣ ከውሃ ላይ ትራንስፖርት ከውሃ ውስጥ ሀብቶችና መዝናኛዎች ጋር ተዛማጅ ያላቸው 14 የፖሊሲ ዓለማዎችን ያስቀምጣል፡፡ በውሃው ዘርፍ ከቀረቡት የሥራ ዘርፎች መካከል ውሃን ለተጠቃሚው ማዳረስ፣ ጥበቃ ማድረግ፣ የውሃ ቴክኖሎጂን ማሻሻል፣ ስለከርሰ ምድር፣ ስለድንበር ተሻጋሪ ውሃዎችና ስለጥቅሙ ተጋሪዎች ጉዳይ ሲይዝ በዘርፍ ዘለል ሥራዎች ውስጥ ስለውሃ አቅርቦትና ንጽህና ስለመኖር፣ ከውሃ ስለሚገኝ የኃይል ምንጭ ያትታል፡፡ ፖሊሲው የኢትዮጵያ የውሃ ችግሮች ምክንያቶች ብሎ ያስቀመጣቸው ከሀገሪቱ ተፈጥሯዊ አቀማመጥና በዝናብ እጥረትና አስተማማኝ አለመሆን ጋር የተያያዙ ብቻ መሆናቸው የችግሮች አተናተኑን ሙሉዕ አያደርገውም፡፡

## 3.5 ድህነትን ለማስወገድ የዘላቂና የተፋጠነ ልማት እቅድ (PASDEP እ.ኤ.አ. 1995)

የተፈጥሮ ሀብትን የሚመለከተው የዚህ እቅድ ክፍል የገጠሩን ልማት በተፋሰስ ደረጃ በመቅረብ ዕድገቱን ለማፋጠን የወጣ ሲሆን ፕሮግራሙቹም ዘላቂ የመሬት አጠቃቀም ማነጅመንት፣ የመስኖ ውሃ ማነጅመንት የአፈርና ውሃ ጥበቃ የደን ሃብት ማነጅመንት የዱር እንስሳት ማነጅመንትን የብዝሐ ሕይወት እንክብካቤና አጠቃቀም የሚሉትን ይይዛል፡፡እቅዱ ከያዛቸው ዝርዝር ሥራዎች ከሚወሰደው ጊዜ ከሚያስፈልገው የፋይናንስና የሰው ኃይል አንፃር በተባለው ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ መሆኑ ቢያጠራጥርም የተነደፉት የሥራ እቅዶች የገጠሩን ልማት ለማፍጠን በተፋሰስ ደረጃ በመቅረብ የተለያዩ የተፈጥሮ ሃብቶችን ተያያዥነት እውነታ መሠረት ያደረገ በረጅም ጊዜ ውጤት ሊያስመዘግብ የሚችል ሰነድ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

## 3.6 የአካባቢ ተጽእኖ መገምገሚያ አዋጅ EIA (እ.ኤ.አ. 2002)

በኢኮኖሚው ውስጥ የሚደረጉ ኢንቨስትመንቶች አካባቢ ላይ የሚያደርሱት ተጽእኖ እየታየ እንዲካሄድ የሚረዳ ሕግ ሲሆን አሁን ከሚታየው ሁኔታ አንፃር አስፈላጊና ወቅታዊ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ይሁንና ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ለማስመዝገብ ካለው እንቅስቃሴ፣ ኢንቨስተሮች ለአካባቢ እንክብካቤ ካላቸው ግንዛቤና በተለይ ይህን ለመቆጣጠር ካለው የባለሙያዎች ውስንነት አንፃር ሲታይ በአጭር ጊዜ ሕጉን ሙሉ ለሙሉ መተግበር አዳጋች ቢመስልም ተጠናክሮ መቀጠል የሚገባው መልካም ጅምር መሆኑ አያጠራጥርም፡፡

## 3.7 የገጠር መሬት አጠቃቀም ፖሊሲና ስትራቴጂ (እ.ኤ.አ. 2004)

ይህ ፖሊሲ መሬት የሕዝብ ነው በሚለው መርሆ ላይ የመሠረተ ነው፡፡ መሬትን የመያዝ፣ የመጠቀምና የማዛወር መብትን የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይዟል፡፡ ከፖሊሲ ሰነዱ ተከትሎ የወጣው የገጠር መሬትን የማስተዳደርና የመጠቀም አዋጁ፣ በእርሻ የሚተዳደር ማንኛውም ሰው መሬት ያለክፍያ የማግኘት፣ ይዞታን የማዛወርና የማከራየትን መብት ጨምሮ የይዞታ ማረጋገጫ መረጃ እንደሚሰጥ ያረጋግጣል፡፡ በውርስ ወይም በስጦታ የገጠር መሬትን የማግኘት መብት በእርሻ ሥራ ላይ ለሚተዳደር ብቻ መፈቀዱ በመጠኑም ቢሆን ከከተማ ወደ ገጠር ሊፈስ የሚችለውን የእውቀትና

የካፒታል ፍሰትና የዜጎችንም የውርስ መብት የሚገድብ እንዳይሆን ቢመርመር መልካም ሲሆን ይህ ፖሊሲ የይዞታ ግዴታና መብት በሕግ ተደንግገው የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ እንዲሰጥ መወሰኑ መንግስት የገጠር ልማቱን ለማፍጠን ከወሰደው ጠቃሚ እርምጃዎች መካከል የሚመደብ ይሆናል፡፡

### 3.8 የዱር እንስሳት ፖሊሲና ሕግ (እ.ኤ.አ. 2005)

ፖሊሲው ለሀገራችን በአይነቱ የመጀመሪያው ሲሆን በመግቢያው የዱር እንስሳትን ጥበቃና ልማት የሀብቱን አጠቀቀም የሕዝቡንና የባለሃብቶችን ተሳትፎ በዘርፉ የመረጃ አሰባሰብን አስፈላጊነት ያካትታል፡፡ የፖሊሲው ዓላማ የሀገሪቱን የዱር እንስሳት ሀብት የመንከባከብ ለኢኮኖሚው ግንባታ ያለውን አስተዋጽኦ ማሳደግ፣ ለመጪው ትውልድ ማቆየትንና ዓላም አቀፍ ስምምነቶችን ማክበር የሚሉትን ያካትታል፡፡ ፖሊሲውን ተፈፃሚ የሚያደርገው የዱር እንስሳት ሕግ ሀብቱን በአራት የከፈለው ሲሆን እነዚህም ብሔራዊ ፖርክ፣ የዱር እንስሳት መጠለያ፣ የዱር እንስሳት ጥብቅ ስፍራና ጥብቅ የአደን ክልል የሚሉትን ያካትታል፡፡ ከዱር እንስሳት ስለሚገኝ ገቢ አጠቃቀም የዱር እንስሳት ውጤቶች ንግድ የፌዴራሉና የክልል አስፈፃሚ አካላት ስልጣንና ኃላፊነትን ቢለይም ፖሊሲውን የማስፈጸምና የገቢዎችን አጠቃቀም በተመለከተ በፌዴራልና በክልል መንግስታት እንዲሁም በሀብቱ ዙሪያ የሚኖረው ሕ/ሰብ ኃላፊነትና ድርሻ በሚወጣው ደንብ ውስጥ በሚገባ መብራራት የሚገባው ይሆናል፡፡

### 3.9 የደን አያያዝና አጠቃቀም ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ሕግ

በሀገሪቱ ታሪክ የመጀመሪያ የሆነው እ.ኤ.አ. የ2007 የደን ፖሊሲ ዓላማ የደን ሀብትን በአግባቡ በማልማት የደን ውጤት ፍላጐት ማሟላትን፣ ደን ለኢኮኖሚው የሚኖረውን አስተዋጽኦ ማሳደግን ሲያካትት ከስትራቲጂዎቹ መካከልም የደን ቴክኖሎጂን ማሳደግ፣ የደን ውጤቶችን ገበያ ማስፋፋትና ለግል ደን አልሚዎች ድጋፍ ማድረግ የሚሉትን ይጨምራል፡፡ በተለይ ለግል ደን አልሚዎች ከሊዝ ነፃ መሬት፣ እስከ ምርት ድረስ ከመሬት ግብር ነፃ ማድረግን በድርድር የመንግስትን ደን ለግል አልሚዎች ማሳለፍንና አልሚው ብድር የሚያገኝበትን ሁኔታ ማመቻቸት የሚሉትን ያካትታል፡፡ ሰነዱ ደን ከሌሎች ዘርፎች ጋር ያለውንም ትስስር ያገናዘበ ነው፡፡ ፖሊሲውን ወደ ተግባር የሚያሸጋግረው ሕግም የወጣው በዚሁ ዓመት ሲሆን በደን ዙሪያ የሰፈረው ሕዝብ በልማቱ ተሳታፊ ሆኖ የጥቅሙ ተጋሪ መሆን እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ሆኖም የግል ደን ለሚያለሙ የሚሰጠው ማበረታች በፖሊሲው ውስጥ የተጠቀሰውን ያህል በደን ሕጉ ሰፍሮ አይገኝም፡፡

### 3.10 ዓለም አቀፍ ስምምነቶች

ኢትዮጵያ ፈራሚ የሆነችባቸው በረሃማነትን የመከላከል፣ የአየር ንብረት ለውጥና የብዝሃ ሕይወት ጉዳይ ስምምነቶች ሲሆኑ እነዚህም የሀገሪቱ ሕግ አካል ተደርገው የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ እ.ኤ.አ. በ1998 የኢትዮጵያ የአካባቢ ባለሥልጣን የስምምነቶቹን ማስፈጸሚያ የተግባር መርሐግብር መንገድ የቀየሰ ሲሆን ስትራቴጂዎችንና እቅዶችን በመንደፍ ያተለያዩ አውደ ጥናቶችንና ሪፖርቶችን በማዘጋጀት እንቅስቃሴ አድርጓል፡፡ በተለይ የብዝሃ ሕይወትን ጉዳይ በተመለከተ ቀደም ሲል የተቋቋመው የኢትዮጵያ የብዝሃ ሕይወት ተቋም ብዙ ተግባሮችን ያከናወነ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁንና ብዙ ሥራዎች እንደሚቀሩ አያጠራጥርም፡፡

## 4. ማጠቃለያ

ምንም እንኳን ሀገሪቱ የታሪኳን ርዝመት የሚመጥን ቋሚና የዳበረ የፖሊሲ ቀረፃና አተገባበር ስልትና ተቋም ለመገንባት ሳትችል ብትቆይም ዛሬ የተፈጥሮ ሀብትና የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ ሕግና መርሐግብር ሰነድ እጥረት አለባት ማለት አይቻልም፡፡ ሁሉንም ዘርፎች ያካተቱ በተደጋጋሚ በተካሔዱ ዐውደ ጥናቶች ዳብረው በይዘት ደረጃ ለብዙ ነቀፋ የማይጋለጡ በርከት ያሉ ሰነዶች ተዘጋጅተዋል፡፡ እንደይዘታቸው በሙሉ ጉልበት ወደ አፈፃፀም ገብተው ቢሆን ኖሮ ሀገሪቱ የአካባቢ አያያዝን በተመለከተ ገና ድሮ ወደ ስኬት የሚወስዳትን አቅጣጫ መያዝ በጀመረች ነበር፡፡

### 4.1. በዝግጅት ሒደትና በይዘት የሚታዩ ክፍተቶች፡-

- በፖሊሲ ቀረፃ ወቅት የየሴክተሩ ችግሮች አተናተን ውስን መሆንና ባዮሎጂያዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ያላቸውን ትስስር አለመመልከት፤
- በተፈጥሮ ሐብት ዙሪያ የባቤትነትና የጥቅም አለመግባባቶች አረዳድ ውስንነት፤
- ፖሊሲ ወቅታዊና ሣይንሣዊ በሆነ መረጃ ላይ የመመስረትን አስፈላጊነት ማሳነስ፤
- የፖሊሲ ዓላማዎችና ስትራቴጂዎች ከሀገሪቱ የሰው ኃይል፣ የፋይናንስና የድርጅት አቅም ኣኳያ ሊለኩና (ረዘም ያለም ቢሆን) የጊዜ ገደብ ሊኖራቸው እንደሚገባ አለማድረግ፤
- የፖሊሲ አፈፃፀምን የክትትልና ግምገማ ሥርዓትን የፖሊሲ ሰነዱ አካል አድርጎ ያለመመልከትና አሳታፊ የቀረፃ ስልት አለመከተል፤
- ለአፈፃፀም የፖሊሲን፣የሕግና የደንብን ትስስር አስፈላጊነት ተገንዝቦ በተከታታይ እንዲወጡ አለማድረግ፡፡

### 4.2. ከአፈፃፀም ጋር የተያያዙ ክፍተቶች፡-

- የአስፈፃሚ አካላት ተደጋጋሚ የመዋቅር መገለባበጥ፤
- መንግስት በአሁን ሁኔታ በተለይ በደን ልማት ሊኖረው የሚገባውን ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት መቀነስ፤
- ፖሊሲዎች ሕጎችና መርሐ ግብሮች ይዘትና የአፈፃፀም ስልት በየደረጃው ባሉ የአስተዳደርና የሴክተር መ/ቤቶች አለመታወቅ፤
- የመረጃ አሰባሰብ ቴክኒካዊ ብቃት አለመኖርና የሰው ኃይል እጥረት፤
- በዘርፎች መካከል ያለው ትስስር በአተገባበር ወቅት አናሳ መሆን ናቸው፡፡

### 4.3. አንዳንድ የመፍትሔ አቅጣጫዎች

ሀ/ በተፈጥሮ ሀብት ላይ የይገባኛልና የአጠቃቀም አለመግባባቶች አንዳንዴም ግጭቶች መነሳታቸው

የተለመደ ነው፡፡ በጥቅም ዙሪያ ምንም አይነት አለመግባባት የሌለበትን ሁኔታ ለመፍጠር ስለማይቻል መሞከርም ጊዜ ማባከን ነው፡፡ ሆኖም አለመግባባቶች ከመስመር ወጥተው ተጠቃሚውንም የተፈጥሮ ሀብቱንም እስኪጐዱ ድረስ መጠበቅ ስህተት ነው፡፡ የአለመግባባቶቹ መንስኤዎች የተሻለ የፖሊሲ አቅጣጫ ለመቅረፅ ስለሚጠቅሙ መንግስትን ጨምሮ በባለድርሻ አካላት መካከል ያለውን የአመለካከት፣ የጥቅምና የዓላማ ልዩነት መረዳት የፖሊሲ ቀረፃው መሰረት መሆን ይገባዋል፡፡ በብዙ ፖሊሲ ቀረፃዎች ውስጥ ይህ አካሄድ ትኩረት ያገኘ አይመስልም፡፡

ለ/ አንድ ፖሊሲ ሊያስወግዳቸው ወይም እንዳይከሰቱ ለማድረግ የሚፈልጋቸውን ችግሮች ምንነት፣ እነሳስ፣ ስፋትና ደረጃ መመርመርና መረዳት የመጀመሪያ ተግባሩ መሆን ይኖርበታል፡፡ የፖሊሲ አማራጮች የሚፈተሹት ችግሮቹ በውል ከተለዩ በኋላ ብቻ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ችግር መስለው የሚታዩ ነገሮች የዋናው የችግሩ መንስኤ ነፀብራቅ እንጂ በራሳቸው ችግር ስለማይሆኑ የፖሊሲ አማራጭ ሲዳሰስ በመሠረታዊ ምክንያቶች ላይ ማተኮር ይገባዋል፡፡ አንዳንድ ፖሊሲዎች /ለምሳሌ የውሃ/ የችግር አረዳዱ የተሟላ አይመስልም፡፡

ሐ/ በተፈጥሮ ሀብት ልማት ውስጥ አንዱ ዘርፍ ብቻውን የሚቆም እንዳለመሆኑ የአንድ ዘርፍ ፖሊሲም ከሌሎች ዘርፎችና ዘርፍ-ዘለል ጉዳዮች ጋር ያለው ትስስር ተለይቶ መታየቱ እጅግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ይህን ማድረግ በተለይ በአተገባበር ጊዜ ተያያዥነት ያላቸውን ዘርፎች በጣምራ በማከናወን ፍሬ ያለውና ወጪ ቆጣቢ ሥራን ማከናወን ይቻላል፡፡ አንዳንዶቹ ፖሊሲዎችና መርሐግብሮች ይህን ጉዳይ በሚገባ ያገናዘቡት ሲሆን ጥቂቶቹ ጥልቀት ይጐላቸዋል፡፡ ሁሉም የየሴክተሩ ፖሊሲዎች የተፈጥሮ ሀብቶች ለእርሻው ሥራ ያላቸውን አስተዋጽኦ አጉልተው ማሳየት ይጠበቅባቸዋል፡፡

መ/ በሀገራችን እንደሚታው የተፈጥሮ ሀብቶች በብዙ ሚሊዮን ለሚቆጠር ሕዝብ የሕይወት መሠረቶች ናቸው፡፡ ስለሆነም የሚወጡት ፖሊሲዎችና መርሐ ግብሮች አሳታፊ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በፖሊሲ ቀረፃ ሂደት ውስጥ "ተሳትፎ" የሚለው ከየት ጀምሮ ምን ድረስ እንደሚሄድ ቀመር (Formula) ባይኖረውም በችግር አረዳድና በመፍትሔ አመራረጥ ላይ የባለድርሻ አካላት ጥቅምና ራእይ እንዲካተት ማድረጉ ዘላቂነትና ተፈፃሚነት ያለውን ፖሊሲ መቅረጽ ያስችላል፡፡ በሀገራችን የፖሊሲ አወጣጥ ሂደት የምንጠቀምባቸው የተለመዱ አውደ ጥናቶች አስፈላጊ ቢሆኑም ከምሁራዊ ትንተና አልፈው የፖሊሲው ውሣኔ በቀጥታ የሚመለከተውን የገጠር ባለድርሻ አይወክሉም፡፡

ሠ/ የተፈጥሮ ሀብት ፖሊሲ አጠቃላይ መመሪያ ተደርጐ ቢቆጠርም በጊዜና በመጠን ተወስነው የሚወጡ ዓላማዎች ያሉት ዓላማውንም ለማሳካት የሚረዱትን ስትራቴጂዎች ያመላከተ ሰነድ ነው፡፡ ከዚህም በላይ የፖሊሲው ይዘት ወደ አስገዳጅነት ተለውጦ ተግባራዊ የሚሆነው ሕግ ሲበጅለትና ሕጉም ዝርዝር መመሪያዎች ሲወጡሉት ብቻ በመሆኑ በዚህ መስክ የሚታዩ ክፍተቶች ብዙ በመሆናቸው ሊዘጉ ይገባል፡፡

ረ/ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አስተዳደር ባልተማከለና አሣታፊ በሆነ የፖለቲካ አወቃቀር እንዲሁም በረጋ የባለቤትነት ይዞታ ውስጥ ማካሔድ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ አካሄድ የገጠሩን ማኅበረሰብና የግል ኢንቨስተሮችን እውቀትና ሀብት በልማት ሂደት ውስጥ እንዲገባ ለማድረግ ይረዳል፡፡ የመንግስት የተቆጣጣሪነት (regulatory) ተግባርም የማኅበራዊ አገልግሎቶችን በማደራጀት ላይ መወሰኑ በመርህ ደረጃ ተገቢ ነው ቢባልም በተለይ የግል ኢንቨስተሩም ሆነ ማኅበረሰቡ በሚገባ ባልተሳተፈበት እንደደን ልማት በመሳሰሉት መስኮች ቀጥተኛ ኢንቨስተር ሆኖ መሳተፍ እጅግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ የፖሊሲዎች ሕጎችና መርሐግብሮች ይዘትና የአፈፃፀም ስልት በየደረጃው ለሚገኙ የአስተዳደር ኃላፊዎችና ሠራተኞች ዘርፍ መሥሪያ ቤት ኃላፊዎችና ኤክስፐርቶች እንዲያውቁት ማድረግና በመገናኛ ብዙሃን መላው ሕዝብ እንዲረዳቸው ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ከግል ይዞታ ስር የሚተዳደሩ የእርሻ መሬቶችና በላያቸው ላይ ካሉት ሀብቶች በስተቀር ሁሉም የተፈጥሮ ሀብቶች በሕገ መንግስቱ መሠረት የሕዝብ ሆነው በመንግስት የሚተዳደሩ መሆናቸው ግልጽ ነው፡፡ ብዙዎቹም ፖሊሲዎች ይህን እንደ መንደሪደሪያ ተጠቅመውበታል፡፡ ይሁንና ፖሊሲዎቹ ይህን የሕዝብ ሀብት በአደራ ተቀብለው የሚያስተዳድሩት አስፈፃሚ አካላት የኃላፊነትና የተጠያቂነት መጠን እስከምን እደሆነ የሚጠቁም ክፍል ያላቸው በወጡ ሕጎችም ውስጥ የኃላፊነት እንጂ የተጠያቂነት አንቀጽ አይታይም፡፡

የተፈጥሮ ሀብትን ምርታማነት በማሳደግ የአካባቢን ደህንነት በመጠበቅ በዘላቂነት መጠቀም ኢትዮጵያን ለመሳሰሉ አገሮች ወሳኝ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ ይህ እንዲሆን የተጥሮ ሀብቱን በመጠቀምና በማልማት መካከል ሊኖር የሚገባውን ሚዛን መጠበቅ አማራጭ የለውም፡፡ ይህን ለማድረግ የሚቻለው ደግሞ በጥናት የተደገፈ የችግር አረዳድና የችግር አፈታት ዘዴዎችን በመጠቀም አሳታፊ በሆነ ሂደት ተቀርፆ በሚፀድቅ ፖሊሲ ድጋፍ ብቻ ነው፡፡ ከዚህም በላይ ፖሊሲው ተግባራዊ እንዲሆን የሚያስፈልጉት የሕግ ድንጋጌዎችና ደንቦች ተዘጋጅተው ሙሉዕ አስተዳደራዊ ድጋፍ ያለው፣ በበቂ የሰው ኃይልና ቁሳቁስ የተደራጀ ስልጣን ከተጠያቂነት ጋር የተሰጠው አካል ሊኖር ይገባል፡፡ ፖሊሲዎችና መርሐግብሮች አስፈፃሚ አካላቱም ጭምር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተፈጥረው የሚኖሩ ሳይሆን የፖሊሲዎቹ አተገባበር እየተፈተሸ ጉድለታቸው እየታረመ በየጊዜው የሚፈጠሩትን የሳይንስ ግኝቶች እያዋሃዱ መጓዝ የሚገባቸው ናቸው፡፡

**(መላኩ በቀለ)**

**ምንጭ፡-** ታዬ አሰፋ (አርታዒ)፣ "የኢትዮጵያ ብሔራዊ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና መርሐግብሮች ጥንቅር"፣ ገፅ 357-396፣ ማጥመ፣ አዲስ አበባ፣ 2001 ዓ/ም

**ምስጋናና ማሳሰቢያ**

ይህ ሰነድ የታተመው በአውሮፓ ሕብረት የገንዘብ ድጋፍ ነው፡፡ ለሰነዱ ይዘት ሙሉ ኃላፊነቱ የደራሲው ሲሆን በምንም ሁኔታ የአውሮፓን ሕብረት አቋም እንደሚያንፀባርቅ ተደርጐ መወሰድ የለበትም፡፡

አድራሻ: የማኅበራዊ ጥናት መድረክ ♦ ፖ.ሳ.ቁ 25864 ኮድ 1000 ♦ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ: 011-629 78 88/91♦ ፋክስ: 011-629 78 89
ኢሜይል: fss@ethionet.et ♦ ድረ ገፅ: www.fssethiopia.org.et